# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 211 ግንቦት 23 2004 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ሳይወገድ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ይካሄዳል ብሎ አያምንም። እንደ ንቅናቄዓችን እምነት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ለማካሄድ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ማስወገድ ይገባል። ይህ ሃቅ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብም ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው ብሎ ያምናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የዘረኛው መለስ ዜናዊን የሰብአዊ መብት አያያዝ የሚያወግዝ መግለጫ አወጣ

በአምባገነንነታቸው እርስ በርስ የሚደጋገፉት የአፍሪካ መንግሥታት ያቋቋሙት የአፍሪካ ሰብአዊና የህዝቦች መብት ኮሚሽን ኢ.ኤ.አ ከአፕሪል 18 ሜይ 2, 2012 ባንጁል ጋምቢያ ላይ አድርጎት በነበረው ጉባኤ የዘረኛውን መለስ ዜናዊ አገዛዝ የሰብአዊ መብት አያያዝ አጥብቆ ከመኮነን አልፎ በአስቸኳይ ይሻሻል ዘንድ መግለጫ ማውጣቱ ታወቀ።

የአፍሪካ ሰብአዊና የህዝቦች መብት ኮሚሽን በአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች በአምባገነን ገዢዎች እንዳይገፈፉ ለመከላከል የተቋቋመ ቢሆንም አፍሪካን የሚያስተዳድሩ የብዙዎቹ አገር መሪዎች ተመሳሳይነት ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት እንዳይችል ሸባ አድርጎት የቆየ ቢሆንም በአንዳንድ አገሮች የሚፈጸሙትን የመብት ጥሰቶች አልፎ አልፎ ለማጋለጥ አንዳንድ ጠንከር ያሉ መግለጫዎችን ሲያወጣ ቆይቶአል። ኢትዮጵያን አገራችንን አስመልክቶ ግን አሁን ያወጣውን አይነት መግለጫ አውጥቶ እንደማያውቅ ሪፖርቱን በቅርበት የሚከታተሉ ምንጮች ይናገራሉ።

ኮሚሽኑ በዘንድሮው 51ኛው አመታዊ ጉባ ኤው ኢትዮጵያን በመሳሰሉ የአፍሪካ አገሮች እየተባባሰ የመጣውን የሰብ አዊ መብት ጥሰቶች ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ በፖለቲካና በተለያዩ ምክንያቶች ዘሳች ላይ የሚፈጸመው ግዲያ ለማስቆም በአፍሪካ ቻርተር አንቀጽ 1 ላይ የሰፈረውን የመኖር መብት ሁሉም የአፍሪካ ሀገራት አገዛዞች እንዲያከብሩና የዘሳችን የመናገር የመሰብሰብና ሃሳብን የመግለጽ ነጻነቶች የሚደነግገው አንቀጽ 5,6,7 እና 9 እንዲከበሩ እንዲሁም መረጃ ለማግኘት ሲባል እስረኞችን በግርፋት የማሰቃየት ተግባር እንዲቆም ፤የሮቢን ደሴት መመሪያ (Robin island Guide lines) እና የፕሬስ ነፃነት በአፍሪካ እንዲከበሩ፤ ነፃና ገለልተኛ የፍትህ ስርዓት በአፍሪካ እውን እንዲሆኑ የመሳሰሉትን ውሳኔዎች አሳልፎአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## እንደ አፓርድ አገዛዝ ዜጎች መታወቂያቸው እየታየ ለእስርና ለእንግልት እንደሚዳረጉ ተገለፀ

ለአማራ ገበሬዎችና ሥራ ፈላጊዎች በኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች መዘዋወር የማይቻልበት ደረጃ ላይ መደረሱ ከየአቅጣጫው የሚደርሱን መረጃዎች ያረጋግጣሉ። የአንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ ልሳን የሆነው ፍኖተ ነፃነት በግንቦት 21 ቀን 2004 ዓም እትሙ እንደዘገበው ከሚዛን ተፈሪ ወደ ዲማ ለሥራ የሚሄዱ ተጓዦች ኬላ ላይ መታወቂያቸው ላይ "ብሔር" በሚለው ቦታ ላይ "አማራ" የሚል የተፃፈባቸውን እስር ቤት ተወርውረዋል።

እስር ቤት ቆይተው ከተፈቱት ውስጥ ለፍኖተ ነፃነት ዝግጅት ክፍል የደረሰባቸውን የገለፁት በሚቀጥለው መንገድ ነበር።

> *"ዲማ በጉልበትህ ሠርተህ የምታገኘው ገንዘብ አለ የሚል መረጃ ስለደረሰን ሥራ ፍለጋ በመጓዝ ላይ ነበርን። ሚዛን ተፈሪ ስንደርስ ለፍተሻ ከመኪና ውረዱ አሉን። ወርደን ለፍተሻ ዝግጁ ሆንን። መታወቂያቸው ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጋምቤላ፣ አፋር የሚል እንዲሳፈሩ ተፈቀደላቸው። አማራ የሚለውን 16 ሰዎች ሰብስበው እናንተ እንድታልፉ አይፈቀድም ብለው ሚዛን ተፈሪ ፖሊስ መምሪያ ወሰዱን። ከዚያም እስር ቤት አስገቡን። ከዚያም ሌላ 20 አማርኛ ተናጋሪዎች ተይዘው ታሰሩ። ምን አጠፋን? ወንጀል ሳንፈጽም ለምን ታስሩናላችሁ? ብለን ስንጠይቃቸው ወደዚያ ከሄዳችሁ ሊደጋ ይደርስባችኋል። ወደዚያ አማራ ሄዶ እንዲሰራ አይፈቀድም ብለውናል።"*

እንዲህ ዓይነት ዓይንያወጣ ዘረኝነት በደቡብ አፍሪቃ አፓርታይድ ከተወገደ ወዲህ የትም የሚገኝ አይደለም። የተወሰኑት እርሶ አደሮች ከሶስት ቀናት እስር በኋላ "ትኬት ቆርጣችሁ ወደ ክልላችሁ አማራ ክልል ተመለሱ" የተባሉ ሲሆን ብዙዎቹ አሁንም በእስር ላይ ናቸው። እነዚህ ወገኖቻችን ወደ ትውልድ መንደራቸው እንዳይመለሱ ገንዘባቸውን ጨርሰዋል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠበትን 21ኛ አመት የንግሥና በአሉን በየመሥሪያ ቤቱ አዳራሾች በስብሰባ አክብሮ ለመዋል ተገደደ

የአገራችንን ጊዜያዊና ዘላቂ ጥቅሞችን ለባ ዕዳን አሳልፎ በመስጠትና በተዘፈቀበት የሃብት ምዝበራ ከቀደምቶቹ ሲነጻጸር ተወዳዳሪ ያልተገኘለት የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የስልጣን ማማ ላይ የተቆናጠጠበትን የዘንድሮውን 21ኛ የንግሥና በዓሉን ለማክበር የተገደደው እንደከዚህ ቀደምቶቹ ህዝቡን በግዳጅ ከቤቱ በነቂስ እንዲወጣ በማስገደድ ሳይሆን ደመወዝ ተከፋይ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ማስተናገድ በሚችሉ የየመስሪያቤቶቹ አዳራሾች ውስጥ ተወስኖ እንደሆነ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዜና ገለጸ።

ወያኔ ላለፉት 21 አመታት ሲከተለው በኖረው የተሳሳተ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፖሊሲዎች ምክንያት ህዝባችን ሊወጣው በማይችል የኑሮ ውድነት ፤የአስተዳደር በደልና የፖለቲካ አፈና ውስጥ ወድቆ የሥርዓቱን እድሜ ለማሳጠር ከምንጊዜውም በተሻለ የሥነልቦና ዝግጅት ላይ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የተከበረው ይህ 21ኛው የወያኔ የድል በአል፤ አገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የብዙዎችን ትኩረት ካለመሳቡም ሌላ ዕለቱን ብዙዎች የስቃያቸው መጀመሪያ ቀን አድርገው እንደሚያስቡት ለማወቅ ተችሎአል።

በዘንድሮው የግንቦት 20 በዓል ላይ የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊና ሌሎች በጸረ ደርግ ትግል ወቅት አጋር የነበሩ አንጋፋዎቹ የወያኔ ኢህአደግ ባለስልጣኖች ንግግር ከማድረግ በመቆጠብ በቅጥረኝነት ከነናቸው ካሰለፉዋቸው የበታች ሹሞች ውስጥ በህዝብ ዘንድ ምንም አይነት ከበሬታና አድናቆት ያልተቸራቸውን እንደ ሬድዋን ሁሴን አይነቶቹን ማሰማራታቸው ትላልቆቹ ባለሥልጣናት በ4ቱም የአገራችን ማዕዘን እየተቀጣጠለ በመጣው ህዝባዊ ተቃውሞ መጠመዳቸውንና መደናገጣቸውን ያመለክታል የሚሉ ወገኖች አሉ።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መለስ ዜናዊ በሱማሊያ ክልል ያሰማራው ልዩ ፖሊስ ሃይል 10 ንጹሃን ዜጎችን በመግደል በበርካቶች ላይ ሰቆቃ መፈጸሙን አለም አቀፉ የሰብ አዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሂውማን ራይትስ ወች አጋለጠ

ታዋቂው የሰብአዊ መብቶች ጠበቃ የሆነው ሂውማን ራይትስ ወች በትናንትናው እለት ባወጣው ዘገባ ፣ የወያኔ አገዛዝ ያስመራው ልዩ የፖርስ ሀይል በምስራቅ የሶማሊ አካባቢ መጋቢት ወር ውስጥ 10 ሰዎችን መግደሉን ፣ ወደ ሱማሊ ላንድ በላከው የአጣሪ ቡድን ማረጋገጡን ገልጧል።

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር መጋቢት 16 የልዩ ፖሊስ አባላት በጋሻሞ ወረዳ ራቅዳ በምትባል መንደር ውስጥ በአንድ ንጹህ የአካባቢው ተወላጅ ላይ አንድ የፓርላማ ተመራጭ የሚያወርደውን ስድብ የተቃወመ ጓደኛው ላይ ልዩ ፖልሲ የወሰደውን እርምጃ በመቃወም ህዝብ በቁጣ ገንፍሎ 7 የልዩ ሀይል አባላትን መግደሉን እንዳረጋገጠ የገለጸው ሂውማን ራይትስ ዎች ልዩ ሀይሉ በወሰደው የአጸፋ እርምጃ ዜጎችን ሰብስቦ ካሰረ በኋላ በቅጥር ሥር ያዋላቸውን 10 ወንዶች ከ እስር ቤት አውጥቶ እንደረሸና ከነዋሪዎች ጋር በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ተጨማሪ 9 ዜጎች መገደላቸውን እንዲሁም 24 ወንዶች ተይዘው መወሰዳቸውን አጋልጦአል። የልዩ ሃይሉ ጥቃት በዚህ ሳያበቃ በአካባቢው የነበሩ የተለያዩ ቤቶችንና ሱቆችንም ተዘርፎአል ብላአል ህወማን ራይትስ ዎች በሪፖርቱ።

የሂውማን ራይትስ ወች የአፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ሌስሊ ሊፍኮው እንደተናገሩት በልዩ ፖሊስ አባላት ላይ የደረሰው ጥቃት፣ በነዋሪው ላይ የደረሰውን ጥቃት ተገቢነት አያመለክትም ። የኢትዮጵያው አገዛዝ በክልሉ ያሰማራው ይህ በህግ የማይገዛ ሃይል በነዋሪዎች ላይ የወሰደው እርምጃ ከህዝቡ ለደረሰበት አጸፋ ተደርጎ የማይወሰድ በመሆኑ ማሰሪያ ሊበጅለት እንደሚገባና ጥቃት ፈጻሚዎቹ ለህግ እንዲቀርቡ ዳይሬክተሯ ጠይቀዋል።

የልዩ ሀይሉ በሶማሊ ክልል ተመሳሳይ አሰቃቂ ግድያዎችን እንደሚፈጽም ሪፖርቱ ያመለክታል። ልዩ ሀይል እየተባለ የሚጠራው ታጣቂ ቡድን ተጠሪነቱ ለማን እንደሆነ ባይታወቅም፣ የኢትዮጵያ መንግስት የትጥቅና ምግብ አቅርቦት እንዲሁም ስልጣንና ደሞዝ እንደሰጣቸው ድርጅቱ አስታውቋል።

ሂውማን ራይትስ ወች መረጃውን ያገኘው ቃለምልልስ ከተደረገላቸው 30 የጉዳቱ ሰለባዎች፣ የተጎጂዎች ዘመዶችና የአካባቢው ነዋሪዎች ነው። መጋቢት 17 የልዩ ፖሊስ ሀይል ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ባደረጉት የተኩስ ልውውጥ 7 የፖሊስ አባላት መገደላቸውን ተከትሎ፣ ወታደሮቹ 23 ወንዶችን በመኪና ጭነው ጋልካ ወደሚባል ቀበሌ ወስደዋቸዋል። በመንገድ ላይ 5 የአካባቢውን ተወላጆች ከመኪና ላይ እንዲወርዱ በማድረግ ረሽነዋቸዋል። መጋቢት 17 ደግሞ አዳዳ በሚባል አካባቢ በሁለት መኪኖች ሲጓዙ የነበሩ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በእምነት እንድንከፋፈል የሚደረግብንን ተንኮል ለማክሸፍ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፍፃሜን አሻግረን እንመልከት!!!

ኢትዮጵያ ውስጥ የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች በመከባበር መኖራቸው እውነት ቢሆንም እንደ ተቋም አንዱ ሌላኛውን ደግፎ ሲነሳ የታየበት አጋጣሚ እምብዛም አልነበረም። እንዲያውም በወያኔ ቆስቋሽነት በሁለቱ የእምነት ተከታዮች መካከል የነበረው መከባበር እየላላ፤ ሽኩቻዎችና የእርስ በርስ ውንጀላዎች እየበረከቱ መጥተው እንደነበር የማይካድ ነው። ይህ ሁኔታ አንድነታችን ላይ ቀላል የማይባል ስጋት ጥሎ ነበር፤ ዛሬም ይህ ስጋት ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ማለት አይቻልም። ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ደግሞ ይህ ስጋት አብሮን መቆየቱ አይቀርም።

ይሁን እንጂ የሙስሊሞች ለመብት ጥያቄዎች መነሳት በአንድነታችን ዘላቂነት ላይ የነበረንን ስጋት ጉልህ በሆነ መጠን እንዲቀንስ ረድቷል። ዛሬ በሁለቱ ሃይማኖቶች መምህራን እና ምዕመናን መካከል ከዚህ በፊት ከነበረው እጅግ የላቀ መቀራረብ እየታየ ነው።

በአንዳንድ ሁኔታዎች የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች ከመከባበር አልፈው መደጋገፍ ጀምረዋል። ለምሳሌ:-

1. በስደት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ የመብት ጥያቄ መሆኑን በመረዳት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ከጎናቸው እንዲቆሙ ጥሪ አድርጓል።
2. የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ተወካዮች በቅዱስ ሲኖዶሱን መግለጫ የተሰማቸውን ደስታ በይፋ ገልፀዋል።
3. ወያኔ በዋልድባ ገዳም ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት በመቃወም በሰሜን አሜሪካ እና አውሮፓ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ከክርስቲያን ወንድሞቻቸው ጎን ቆመው “ዋልድባ ታሪካዊ ቅርሳችን ነው፤ መደፈር የለበትም” እያሉ ድምፃቸውን አሰምተዋል።
4. በደቡብ አፍሪቃ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ደጋፊዎች በጠሩት ስብሰባ ውስጥ አንድ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መምህር ሙስሊም ኢትዮጵያን ለሚያደርጉት ተጋድሎ አጋርነት ለመግለጽ “ሁላችን በአንድ ቃል ፈጣሪን እናመስግን” በማለት “አላሁ አክበር!” ሲሉ የአዳራሹ ተሰብሳቢ በሙሉ አፃቸው “አላሁ አክበር” ብሏል።

እነዚህ ነገሮች ለአገራችን አንድነት እና ለአብሮነታችን ከፍተኛ ማኅበራዊ ዋጋ ያላቸው ተግባሮች ናቸው። እነዚህ መቀራረቦች ለዛሬው ትግላችን አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ብቻ ሳይሆን ለወደፊቷ ኢትዮጵያም ጠንካራ የመሠረት ድንጋዮች ናቸው።

አዎ! የኢትዮጵያ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ እያቀረበ ያለው ጥያቄ የሙስሊሙ ብቻ አይደለም። የሙስሊሙ ጥያቄ ራሳቸውን የሚያከብሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጥያቄ ነው። የሙስሊሙ ጥያቄ ለወያኔ ባርነት ለመገዛት ፈቃደኛ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጥያቄ ነው። ከላይ እንደተገፀው ለመብቶቻችን ስንታገል ከትናንሽ የእርስበርስ ቅራኔዎች ወጥተን ስለጋራ ጥቅሞች ወደ ማሰብ የምንሸጋገር መሆኑ ደግሞ ለመተባበራችን ተጨማሪ ምክንያት ነው።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የማይጠቀመው ወያኔ ብቻ ነው። የወያኔ እድሜ የረዘመው ኢትዮጵያዊን በተለያዩ ምክንያቶች በመከፋፈላችን እንደሆነ ለብዙዎች ግልጽ ነው። እናም ወያኔ ይኸንን በማበብ ላይ ያለን ኅብረት በእንቡጡ ለመቅጨት እየተሯሯጠ መሆኑ ሊገርመን አይገባም። ከእነዚህ ጥረቶቹ አንዱ የአሁኑ በካድሬዎች የተሞላው የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት (መጅሊስ) ፈርሶ በካድሬዎቹ የተሞላ ሌላ መጅሊስ ለመፍጠር የሚያደርገው መሯሯጥ ነው። ወያኔ “በሃይማኖት ጉዳይ እጄ አስገብቼ አላውቅም” እያለ ሲምል እነደነበር የሚታወቅ ነው። ሆኖም ግን የሕዝበ ሙስሊሙ ቁርጠኝነት በተወሰነ መጠን እንዲያፈገፍግ በማስገደዱ ሲናገረው የነበረውን ረስቶ፣ የተጠላውን መጅሊስ አፍርሶ ሌሎች ካድሬዎቹን በአዲስ የመጅሊስ አመራርነት ለማስመረጥ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

በወያኔ አስፈፃሚነት የሚደረጉ ምርጫዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ ምርጫ 97 እና ከሱ በባሰ ደግሞ ምርጫ 2002 አሳይተውናል። ወያኔ ምርጫን ማበላሸት፣ ድምጽ መዝረፍ እና ተወዳዳሪዎችን ማሸማቀቅ እንጂ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ አይችል። ይህ ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው። ስለዚህም በወያኔ አስፈፃሚነት የሚደረግ ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም። የምርጫው አስፈፃሚ ወያኔ እስከሆነ ድረስ ምርጫው መስጊድ ውስጥ ተደረገ ቀበሌ እጅግም ልዩነት አይኖረውም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ሳይወገድ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ይካሄዳል ብሎ አያምንም። እንደ ንቅናቄዓችን እምነት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ለማካሄድ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ማስወገድ ይገባል። ይህ ሃቅ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብም ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው ብሎ ያምናል።

ስለሆነም መላው ነፃነት ናፋቂው ኢትዮጵያዊ የሃይማኖት ድንበር ሳይገድበው ከሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ጎን በመቆም ለነፃነት፣ ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለእኩልነት እንዲታገል ግንቦት 7 ጥሪ ያደርጋል። የጉዞዓችን አቅጣጫም የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አምባገነን አገዛዝን ወደ ማስወገድ እንዲያመለክት ያሳስባል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ “በእምነት እንድንከፋፈል የሚደረግብንን ተንኮል ለማክሸፍ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፍፃሜን አሻግረን እንመልከት!!! ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

.........................................................................................................................................

## የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የዘረኛው መለስ ዜናዊን የሰብአዊ መብት አያያዝ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

51ኛው የባንጁል ጉባኤ ከአስራ ሁለት ቀናት በላይ የየሀገሩን የሰብአዊ መብት አያያዝ በእጅጉ ከመረመረ በኋላ ኢትዮጵያ አገራችንን ከፍተኛ የመብት ጥሰት ከፈጸሙ አገሮች በዋኝናዎቹ ተርታ ሲያስቀምጥ ሞሪሽስ፣ ጋና፤ ቦትስዋና የመሳሰሉትን ሀገራት የሠብአዊ መብት አያያዝ አድንቆአል።

ኢትዮጵያን አስመልክቶ ኮሚሽኑ ባወጣው መግለጫ አገሪቱ ውስጥ እየተፈጸመ ያለው የመብት ረገጣ እጅግ እንደሚያሳስበው ገልጾአል። በአሳሳቢነታቸው የተጠቀሱት ጥሰቶች በዝነኛው የማእከላዊ የወንጀል ምርመራ ውስጥ እስረኞች ላይ በጭካኔ የሚፈጸመው ሰቆቃ፤ የፖለቲካ እስረኞች ገለልተኛ የሆነ ዳኝነት የሚያገኙበት ሥርዓት አለመኖር፤ በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ በህግ ባለሙያዎችና በቤተሰቦቻቸው እንዳይጎበኙ መከልከል ዋናዎቹ ሲሆኑ ዜጎች ባልታወቁ እስር ቤት እየታጎሩ ሰቆቃ እንደሚፈጸምባቸውም አትቶአል።

ከዚህም በተጨማሪ በሠላማዊ የፖለቲካ ትግል ስልት ሥርዓቱን ለመለወጥ በግንባር ቀደም ተዋናይ የሆኑ ሠላማዊ ታጋዮችንና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በመጠቀም ስርዓቱን የተቹ ጋዜጠኞችን በአሸባሪነት መወንጀል እጅግ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶአል የሚለው የኮሚሽኑ ሪፖርት፤ የጾታና የሰብአዊ መብት ጥበቃ ተከራካሪዎች አገሪቱ ውስጥ እንደ ልብ መንቀሳቀስ እንዳይችሉ በአዲሱ የበጎ አድራጎት ህግ ተቀፍድደው ለጥቃት እንደተዳረጉ በመግለጽ እርምጃውን ኰንኖአል፡፡

በባጁል ጉባ ዕውን ያካሄደው የአፍሪካ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የወያኔን አገዛዝ ሰብአዊ መብት ረገጣ ለመጀመሪያ ጊዜ አጥብቆ በኰነነበት የዘንድሮው መግለጫ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፎአል፤

1. በአፍሪካ ቻርተር አንቀጽ 16 መሠረት በታወቁ እስር ቤቶች ወይም በሌላ ቦታ የሚገኙ ታሳሪዎች በገለልተኛ አጣሪዎች በቤተሰቦቻቸውና በህግ አማካሪዎቻቸው እንዲጎበኙ እንዲሁም በቂ የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ፡፡
2. ባልታወቁ እስር ቤቶች የሚገኙ ታሳሪዎች እውቅና ባላቸው ማረሚያ ቤት እንዲገቡና አስቸኳይ ፍትህ እንዲሰጣቸው
3. የኢትዮጵያ መንግስት የሮቢን ደሴት መመሪያ ጨምሮ ስለ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የእስረኞችን አያያዝ በተመለከተ ለዳኞችና ለእስር ቤት አስተዳዳሪዎች ተከታታይ ስልጠና እንዲሰጥና በዳኝነት ነፃነት ጣልቃ ከመግባት እንዲታቀብ;
4. አሳሪዎን አዲሱን የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ህግ ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ አንፃር መልሶ እንዲቃኘው
5. እ.ኤ.አ በ2008 እና 2009 የወጡት የሚዲያና የፀረ አሸባሪነት ህጎች ላይ የሠፈሩት አንዳንድ አንቀፆች ሀሳብን በነፃነት ለመግለጽ ደንቃራ በመሆናቸው እንዲሰረዙ የሚሉ ናቸው፡፡

## መለስ ዜናዊ በሱማሊያ ክልል ያሰማራው ልዩ ፖሊስ ሃይል 10 ንጹሃን ዜጎችን በመግደል በበርካቶች ላይ ሰቆቃ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የልዩ ሀይል አባላት ተኩስ በመክፈት 4 ነዋሪዎን ገድለዋል። የአካባቢው ነዋሪዎች ሟቾችን ለመቅበር ወደ ቀብር ስፍራ ሲሄዱ የልዩ ሀይሉ ፖሊስ አባላት ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር የተኩስ ልውውጥ አድርገው አምስት ነዋሪዎችን ገድለዋል። ልዩ ሀይሉ አራት ነዋሪዎች በመያዝ እረሸነዋቸዋል። አንድ ሴት የእንስሳት ሀኪም የነበረው ወንድሟን ፖሊሶቹ ከቤት አስወጥተው ግንባሩ ላይ ከተኮሱበት በሁዋላ ጉሮሮውን ቆርጠውት ሄደዋል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኦጋዴን ለሚፈጸመው የስብአዊ መብቶች ጥሰት የሚሰጠው መልስ ፣ አካባቢውን ለጋዜጠኞች እና ለሰብአዊ መብት ድርጅቶች በመዝጋት ነው ሲል ደርጅቱ ኮንኗል። ድርጅቱ ለጋሽ አገራት የኢትዮጵያ መንግስት አካባቢውን ለጋዜጠኞችና ለሰብአዊ መብት ድርጅቶች ክፍት እንዲያደርግ ተጽኖ እንዲያሳርፉ ጠይቋል።

## አላሁ አኩበር !!! እግዚአብሄር ታላቅ ነው !!!

አላሁ አኩበር !!! እግዚአብሄር ታላቅ ነው!!! ሰሞኑን ጎልተው የምንሰማቸው የህዝቡ መፈክሮች ናቸው።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄም ከህዝቡ ጋር ሁኖ አላሁ አኩበር፤ እግዚአብሄር ታላቅ ነው ይላል።

አዎን እግዚአብሄር ታላቅ ነው። በወንድሞች መካከል ሲዘራ የከረመው የጠብ ዘር ፍሬ እንዳያፈራ ያደረገው እግዚአብሄር በእውነት ታላቅ ነው።በመለስ ዜናዊ የተዘራውን የጥላቻ ዘር ፍሬ እንዳያፈራ በዚህ ክፉ ዘመን ጎን ጎን ለቆሙ፤ እጅ ለእጅ ለተያያዙ ኢትዮጵያዊያን ክርስትያኖችና ሙስሊሞች ምስጋናችንና አክብሮታችን ይደረሳቸው።

ሰሞኑን ኢትዮጵያዊያን አንድ ሁነው በአንድ ቋንቋ የህግ የበላይነት ይከበር፤ ፍትህ ይንገስ፤ እኩልነት ይምጣ፤ በሃይማኖታችን ውስጥ ጣልቃ አትግቡ እያሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እየጮሁ ነው።

ለዚህ ጩኸት ከመለስ ዜናዊ የተሰጠው ምላሽ "ውሾችም ይጮኻሉ ግመሏም ትሄዳለች" የሚል ሁኗል። ከዚህ ጨካኝ ግለሰብ እና በዙሪያው ከተሰባሰቡ ምናምንቴዎች ከዚህ ውጪ የሚጠበቅ በጎ ምላሽ ይኖራል ብለን አንጠብቅም።

የመለስ ዜናዊ ወዳጅ የነበረው የሊቢያው ጋዳፊም ህዝቡ "አላሁ አኩበር" ብሎ በጮኸ ግዜ ህዝቡን "አይጥ" እያለ ሲሳደብ ሰምተነው ነበር። ዛሬም መለስ ዜናዊ ህዝቡን በውሾች፤ ራሱን ደግሞ በግመል መስሎ የስድብ አፉን ከፍቶ "ውሾች ይጮኻሉ ግመሎችም ይሄዳሉ" ሲል ሰማነው።

መለስ ዜናዊ ዓይን እያለው የማያይ፤ ጆሮም እያለው የማይሰማ እግዚአብሄርን የማያውቅ ፤ሰውንም የማያፍር ክፉ ግለሰብ መሆኑን ድርጊቶቹ በሙሉ ቋሚ ምስክሮች ናቸው። በአገራችን ታሪክ እንደመለስ ዓይነት ውሸታም፤ እንደመለስ ዓይነት ጨካኝና ፈሪ፤ እንደመለስ ዓይነት ዘራፊ ታይቶ አይታወቅም።

በአገራችን ውስጥ ብዙ ነገስታት ነግሰዋል።በግዜአቸው ወቅቱና ሁኔታው በሚፈቅድላቸው ሁሉ አገሪቷን ለማስተዳደር የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። መለስ ዜናዊን ካለፉት ነገስታት ጋር ማወዳደር እንደ አንድ የዋህና ቅን አምባገነን ስለሚያስቆጥረው ካለፉት ነገስታት ጋር ማወዳደር ተገቢ አይሆንም። የሆኖ ሆኖ እንደ መለስ ዜናዊ አይነት ውሸታም ታይቶ አይታውቅም። መለስ አፍን ለጎሙ በያዘው ፓርላማ ውስጥ ቀርቦ የሌለውን አለ፤ያለውን ደግሞ የለም ሲል የሚያፍር አይደለም። ዛሬ ከሃይማኖታችን ላይ እጅህን አንሳልን ያሉ ሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን አልቃይዳንና አልሸባብን ከመሳሰሉ ዓለም አቀፍ አሸባሪዎች ጋር አስተሳስሮ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ፍላጎት ያላቸው ናቸው ብሎ ተናግሯል። ይሄ ግን እውነት አይደለም። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ አንድ እና አንድ ነው። "መለስ ዜናዊ ከሃይማኖታቸው ላይ እጁን እንዲያነሳ እና የሃይማኖት መሪያቸውን የመምረጥ መብት እንዲከበርላቸው። "ጥያቄው ይሄ ሁኖ ሳለ አንደበቱን ለጉሞ በያዘው ሙት ፓርላማ ውስጥ ሆኖ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ፍላጎት ያላቸው አክራሪ ሃይሎች ናቸው ማለቱ ከውሸቱ በላይ ለህዝቡ ያለውን ንቀት የሚያሳይ ነው። የዚህ ነገር ጉድይ በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም።

ይህ አባባል ገደብ የሌለው የጭካኔው መገለጫም ጭምር ነው። ሙስሊሙንና ክርስትያኑን አጋጭቶ በንጹሃን ደም ላይ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ካለው ከንቱ ምኞት የሚነሳ መሆኑ አሁን ለሁሉም ግልጽ ሁኗል። ለመለስ ዜናዊ የአዲስ አበባ ወይም የአርሲ ኢትዮጵያዊያን ደም ከሃውዜን ህዝብ ደም ጋር የሚተካከል አይደለም። የሃውዜንን ህዝብ ለማስጨፈጨፍ ወደ ኋላ ያላለ ለሌሎች ኢትዮጵያዊያን የሚራራ ልብ ይኖረዋል ማለት ሞኝነት ብቻ ነው። ይሄን በአግባቡ የተገነዘቡ ኢትዮጵያዊያን ዛሬ እጅ ለእጅ ተያይዘው ለመብታቸው አብረው እየጮሁ ነው። ይሄን የነጻነት ጩኸት "የውሾች ጩኸት" ብሎ ለሚሳደብ ዘረኛና ዘራፊ አገራችንን ሰጥተን ዝም የምንልበት ግዜ አይደለም።

ከመለስ ዜናዊ እጅ አንድነትንና ነጻነትን በነጻ ማግኘት የሚቻል አይደለም። ከዚህ ፈሪና ጨካኝ ግለሰብ አጅ ነጻነትን ለማግኘት የሚደረግ ትግል ብዙ መስዋእትነትን የሚጠይቅ ተግባር ነው። መለስ ዜናዊና ዘባተሎ ተከታዮቹ ነጻነት የሚለውን ድምጽ በሰሙ ቁጥር በጦር እንደተወጋ አውሬ የሚደነብሩ የሚቆጡ በመሆናቸው ብዙ ጥፋት ሊያደርሱ እንደሚችሉም መገነዘብ ያስፈልጋል። ምግባራቸው የፈጠረባቸው ፍርሃታቸው፤ከፍርሃታቸውም የሚመነጨው ጭካኔያቸው የሚያመጣውን ክፉ ድርጊት ለመቋቋም የሚያስችል ህብረት ከምን ግዜውም በላይ አስፈላጊ ሁኗል።ተባብረን እንስራ ስንል የነመለስ ዜናዊን የጭካኔ በትር የምናቋቋምበትን ኃይል ለማግኘትና ለሁላችን የምትሆን አገር ለመፍጠር ወሳኝ ነገር ስለሆነ ነው።

ስለዚህ ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ አንድ ሆነን መለስ ዜናዊንና ዘረኛና ዘራፊ ቡድኑን ከማፋለም ወደ ኋላ አንልም። በመስኪዶቻችን ውስጥ እንፋለማቸዋለን፤ በየቤተክርስትያኖቻችን ውስጥ እንፋለማቸዋለን፤ በአዳራሽ ውስጥ እንፋለማቸዋለን፤ በየመንገዱም እንፋለማቸዋለን። በመለስ ዜናዊ የተነጠቅነው ነጻነታችን እስከሚጠበቅ፤ በዘረኞች የተገደበው እኩልነታችን እስኪመለስ፤ በአገራችን ውስጥ የሚካሄደው ዝሪፊያ እስኪያቆም፤ጥቂቶች ብዙሃኑን ተጭነው፤ ብዙሃኖች ጥቂቶችን ተሸክመው የሚኖሩበት ሥርዓት እስኪፈርስ ድረስ በሁሉም መስክ የጀመርነውን ትግላችንን ከመቸውም ግዜ በላይ አጠናክረን እንቅጥላለን።

በመጨረሻም አላሁ አኩበር !!! እግዚአብሄር ታላቅ ነው !!!! እናሸንፋለን !!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!!**

................................................................................

## ደቡብ አፍሪካ ውስጥ መለስ ዜናዊን በተናጋሪ እንግዳነት ጋብዞ የነበረው የታቦ ኢምቤኪ የአፍሪካ አመራሪ እንስቲቱይት ግብዣውን ሰረዘ። ይህ ለመለስ ዜናዊ በሳምንት እድሜ ውስጥ ሁለተኛ ውርደት ነው ተብላአል

ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚገኘው የታቦ ኢምቤኪ የአፍሪካ የአመራር እንስቲቲዩት በተጋባዥ እንግዳነት ንግግር እንዲያደርግ ጋብዞት የነበረው አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ ለተጋበዘበት ስብሰባ አረአያነት የሚሆን ምንም ቁምነገር ለመናገር የማይችል ወንጀለኛና ነፍሰገዳይ መሆኑን ለማጋለጥ በዚያች አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ስደተችና የሲቪክ ማህበራት በጋራ ባደረጉት ተቃዉሞ ሰፍል ግብዣው መሰረዙን የግንቦት 7 ተባባሪ ዘጋቢ ከጆሃንስ በርግ በላከው ሪፖርት ገለጸ።

በታቦ ኢምቤኪ ሥም የተሰየመው የአፍሪካ የአመራር ኢንስቲትዩት የተባለ ድርጅት በየአመቱ በሚያዘጋጀዉ ዝግጅት ላይ የተለያዩ የአፍሪካ መሪዎችና ምሁራን እየተጋበዙ ንግግር እንደሚያደርጉ የታወቀ ሲሆን በዘንድሮው የንግግር ፕሮግራም ላይ ከተጋበዙት መሃል መለስ ዜናዊ አንዱ መሆኑ እንደታወቀና የርሱ አጭር የህይወት ታሪክ በማስታወቂያ መልክ ለህዝብ ከተነገረ በኋላ በሁኔታዉ የተበሳጩ ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ዜናውን በመቀባበል ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ እንዳዘጋጁ፤ ጋባዦቹም በተደረገው ተቃውሞ ሰልፍ ተደናግጠው ግብዣውን ለመሰረዝ እንደተገደዱ ገልጾአል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቮዥን ዜናውን ለማጣራት ባደረገው ክትትል የዝግጅቱ ኃላፊ የሆኑትን ሚስተር ላኪ ፎሳን አነጋግሮ በኢትዮጵያዊያኑ ተቃውሞ ምክንያት የመለስ ዜናዊ ፕሮግራም እንደተሰረዘና በምትኩ ሌላ ተናጋሪ እንደተመደበ ይፋ አድርጎአል።

ዘረኛዉ መልስ ዜናዊ በዚህ አመታዊ ዝግጅት ላይ ተገኝቶ የተለመዱ ዉሸቱን እንዳይደረድር ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱ ግለሰቦች ዉስጥ አንዱ የዝግጅቱ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል የሆኑትና በአንድ የደቡብ አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ በመምህርነት የሚያገለግሉት ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬ እንደሆኑ የገለጸው ኢሳት እኚህ አገር ወዳድ ምሁር እሳቸዉ አዘጋጅ በሆኑበት አህጉር አቀፍ ጥናታዊ ስብሰባ ላይ መለስ ዜናዊን የመሰለ ሰዉ በተናጋሪነት መጋበዝ የእኔንም የአገሬንም ክብር ያጎድፋል ብለዉ የአዘጋጅ ኮሚቴዉን ሲወተውቱ እንደነበረና በመጨረሻም ከተለያየ አቅጣጫ በተነሳ ተቃውሞ የመለስ ዜናዊ ዝግጅት መሰረዙንና እሳቸዉም በዚህ እጅግ ደስ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## እንደ አፓርድ አገዛዝ ዜጎች መታወቂያቸው እየታየ ለእስርና ለእንግልት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

"የቀን ሥራ ሠርተንም ጉርጓድ ቆፍረንም ህይወታችንን እንቀይራለን ብለን ጉዞ ጀምረን የነበረው። ሆኖም ግን አማራ በመሆናችን ተዘዋውረን ሠርተን እንዳንበላ ተደርገናል።" ሲሉ ተበዳዮች አማረዋል። በመቀጠልም "እኛ ታስረን መፈታት ችለናል። ዛሬም ሥራ ፍለጋ ወደ ምንፈልግበት እንድንሄድና በነፃነት ከቦታ ቦታ እንድንቀሳቀስ አልተፈቀደልንም። ህጋዊን መንገድ ትተው በእግራቸው ጫካ ለጫካ ጉዞ የጀመሩ በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፤ በአውሬ ተበልተዋል። ሲገደሉም በአውሬ ሲበሉም የአካባቢው ኃላፊዎች ምንም የሚሰማቸው ፀፀት የለም። ህገ ወጦች ናቸው። እንኳን ሞቱ እንኳን ተበሉ እያሉ ሲሳለቁ ይሰማል።" ካሉ በኋላ "የሚመለከተው የመንግስት አካል ጉዳዩን በጥሞና ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጠን። ተዘዋውረን የመኖርና ሠርቶ የመብላት መብታችን እንዲከበርልን አሳውቁልን።" በማለት ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

እየተባባሰ የመጣ ዘረኝነት ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው ውስጥ ተዘዋውረው መሥራት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። በቅርብ ዓመታት ወዲህ በረሃና ባህር አቋርጠው የሚጓዙ ስደተኞች የመብዛታቸው አንዱ ምክንያት ዜጎች በአገራቸው ውስጥ ተዘዋውረው መሥራት አለመቻላቸው ነው።

ወያኔ በተለያዩ ምክንያት ህዝብን ከህዝብ እያጣላ ለሃያ አንድ ዓመታት ገዝቷል። እንዲህ ዓይነቱ ውርደት እንዲያበቃ ህዝብ በቁርጠኝነት ወያኔን ይኖርበታል የሚሉ ወገኖች ብዙዎች ናቸው።

................................................................................

## ወያኔ የአደንዛዥ እጾች ዝውውርና የጫት ንግድ በመላው አገሪቱ እንዲስፋፋ ሆን ብሎ እየሰራ መሆኑ ተዘገበ

ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ወዲህ በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የአደንዛዥ እጾች ዝው ውር በመላው አገሪቱ ውስጥ እየተስፋፋ መሆኑንና ይህም ወጣቱ ትውልድ በተለያዩ ሱሶችና እጾች በመደንዘዝ ከአገሩ ፖለቲካ እንድርቅ ለማድረግ ሆን ተብሎ የታሰበ እንደሆነ ተገለጸ።

በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ ቁጥጥር የሚደረግባቸው እጾች በአድስ አበባ የቦሌ አለም አቀፍ አውሮጵላን ማረፊያ በኩል ያለምንም ችግር ወደ አውሮፓና መካከለኛው ምስራቅ አገሮች እንደሚተላለፍ የሚናገሩ ሃይሎች የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በእጽ ዝውውሩ ውስጥ እጃቸው ሳይኖር እንደማይቀር ሳይታለም የተፈታ ነው ይላሉ።

ቀደም ሲል ከምዕራብ አፍሪካና ሩቅ ምስራቅ በኢትዮጵያ በኩል ይተላለፍ የነበረው እንደ ኦጵዬም የመሳሰሉ ከፍተኛ እጾች በአሁኑ ሰዓት አገራችን ውስጥም እየተመረቱ እንደሆነ ይነገራል። ይህ በዚህ እንዳለ የጫት ንግድ በሀገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ ባሉ የትምህርት ተቋማት እና የልጆች መዝናኛ ስፍራ ሳይቀር እጅግ እየተበራከተ መምጣቱን ለማወቅ ተችሎአል።

የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ በዚህ ሳምንት እትሙ እንደዘገበው የጫት ንግድ ቀደም ሲል ባልተለመዱ የአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቦታዎች ተስፋፍቶአል። ስለጉዳዩ የተጠየቁት የጫት ነጋዴዎች ለመስፋፋቱ ዋናው ምክንያት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የቁጥጥር ኬላዎች የነበሩት በመነሳታቸውና መንግስት የጫት ንግድን በማበረታታቱ እንደሆነ ተናግረዋል ብሎአል ፍኖተ ነጻነት፡፡

የንግድ ሚኒስቴር የጫት ኬላዎች መነሳትና አስፈላጊነትን አስመልክቶ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ የሆነው አብዱራሂም የተባለ ሰው "አላስፈላጊ እንግልትና ውጣ ውረድን ለማስቀረት ኬላዎች ተነስተዋል" ሲሉ ምላሽ እንደሰጠ የዘገበው ጋዜጣ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች መንግሥት የጫት ንግድን በከተሞች ላይ መስፋፋቱን ለምን እንደፈለ አልገባንም፤ ልጆቻችንም በቀላሉ ማግኘት በመቻላቸው የጫት ሱስ ሰለባ እየሆኑ ነው፣ በማለት እያማረሩ መሆናቸውን ገልጾአል።

## በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠበትን 21ኛ አመት የንግሥና በአሉን በየመሥሪያ ቤቱ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሬድዋን ሁሴን ወያኔ ኢህአደግን በመወከል ስለበአሉ በሰጠው መግለጫ ተመዝግቦአል ያላቸውን የልማት እድገት በማስረጃ ለማስረገጥ መለስ ዜናዊ አለም አቀፍ ገጽታውን ለማሳመርና በለጋሾች ዘንድ ታማኝነት ለማግኘት ሲል እያስፈበረከ የረጨውን የተጭበረበረ የእድገት ስታቲስቲክስ አንብበው መልሰው የሚያስተጋቡትን ምዕራባዊያን በዋቦነት መላልሶ ሲገልጽ ተስተውላአል።

ወያኔ ባለማቋረጥ የሚዶሰኩረው ልማትና እድገት በአገራችን ተመዝግቦ ቢሆን ኖሮ የእድገቱ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ የሆነው ህዝባችን ቁጭ ብሎ የህብረተሰባችንን የዕለት ተዕለት ኑሮ አስመልክቶ ምንም መረጃ የሌላቸውን የባህር ማዶ ሰዎች ምስክርነት መጥራት ባልተገባ ነበር የሚሉ ወገኖች ከግማሽ በላይ የሆነው ህዝባችን በቀን አንድ ጊዜ እንኳ መመገብ ቅንጦት ያህል እየራቀው በሄደ ቁጥር ነጋ ጠባ እየተለፈፈ ያለው የልማትና የዕድገት ዜና ለወያኔ ካስገኘለት ወዳጅ ይልቅ ያፈራበት ጠላት እያደገ መምጣቱን ይገልጻሉ።

ህዝብ እየተራበ ጠግቦአል፤ እየደሄየ ኑሮው አድጎአል፤ እየታፈነና እየታሰረ ነጻነት በነጻነት ሆኖአል በማለት እራሳቸውንና ተከታዮቻቸውን ሲያሞኙ ከኖሩ የሰሜን አፍሪካ አምባገነኖች ምንም ትምህረት ያልገበየው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በውረደት ለስደት እንደተዳረገው የቱኒዚያው ቤን አሊ፤ በስተርጅናው ለእስር እንደተዳረገው የግብጹ ሆሴን ሙባረክና በራሱ እብሪትና ጥጋብ ጦሱ ለልጅ ልጆቹ እንደተረፈው እስከነ ልጅ ልጆቹ የልጅ ልጆቹን ጭምር ካጠፋው የሊቢያው ጋዳፊ የእጁን የሚያገኝበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ብዙዎች እርገጠኞች ናቸው።

ወያኔ በየአመቱ የሚያከብረው የግንቦት 20 በአል በብዙዎች ዘንድ ባለፉት 21 አመታት ህዝባችን ላይ በተፈጸመው ግዲያ ፤እስራትና እንግልት ምክንያት እንደታላቅ የሃዘን ቀን ይቆጠራል።

በተያያዘ ዜና ወያኔ ኢህአዴግ የጥፋት ሀይሎች ያላቸውን በዝምታ እንደማያይ መግለጹ ታውቆአል።

ወያኔ ሥልጣን የተቆናጠጠበትን 21ኛ የግንቦት20 በአልን ምክንያት በማድረግ ባወጣው መግለጫ ተቃዋሚዎች ያላቸው ሃይሎች በህብረተሰቡ ውስጥ እየፈጠሩ ያለውን ተጽእኖ በዝርዝር አቅርቧል።

"አገሪቱ የተያያዘችው ፈጣን ልማትና የዳበረ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ያስደነገጣቸው የጥፋት ሀይሎች ከውጭ ሆነው ለኢትዮጵያ ድጋፍ አታድርጉ፣ ብድር አትፍቀዱ ከማለት ጀምሮ ከሻዕብያ መንግስት ስልጠናና ምክር በመውሰድ በሽብር ስራ ላይ መሰማራታቸውን፣ በአገር ውስጥ ደግሞ የሀይማኖት፣ የኑሮ ውድነቱንና ሌሎች አጀንዳዎችን በማራገብ ላይ ይገኛሉ" የሚለው የወያኔ መግለጫ የእነዚህን አፍራሽ ሀይሎች ተልእኮ በቸልታ እንደማይመለከት ፣ ህዝቡም ይጥፋት ሀይሎችን በጽናት ለመታገል ከጎኑ እንዲሰለፍ የተለመደውን የቁራ ጩሄቱን አስምቶአል።

ከኢህአዴግ ምክር ቤት የተሰጠው መግለጫ ሀገሪቱ በፈጣን የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ብትገኝም ድህነትና ኋላቀርነት፣የኑሮ ውድነት፣በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታየው በአቋራጭ የመክበር አስተሳሰብና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ሥርዓቱን የሚፈታተኑ ችግሮች ናቸው ሲል በየደረጃው የተቀመጡ የራሱ የፖለቲካ ሹመኞች በህዝብና በአገር ሃብት ላይ የሚፈጽሙትን ወንጀሎች ህዝቡን ግራ ለማጋባት በሌላ ሃይል የሚፈጸሙ አስመስሎ ለማቅረብ ጥሮአል።

ህዝቡ በአገዛዙ ላይ ያለውን ተስፋ አሽመድምዶ የገደለውን እነዚህ ችግሮች ዘላቂ ልማትና መልካም አስተደደርን በማስፈን ሊፈቱ እንደሚችሉ የገለጸው የወያኔ መግለጫ አጣዳፊ የሆኑ የህዝቡን የኑሮ ውድነት ችግሮች ለመፍታት መሠረታዊ የፍጆታ ሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብና የሥራ ዕድሎችን በስፋት በመፍጠር የህብረተሰቡን የመግዛት አቅም ለማሳደግ ኢህአዴግ ትኩረት ሰጥቶ በመረባረብ ላይ ይገኛል ሲል ባለፉት 21 አመታት ያላከናወነውን ተግባር ከአሁን ቦኋላ ሊያከናውን እንደተዘጋጀ የተለመደውን የውሸት ተስፋ ለመስጠት ሞክሮአል።

ኢህአዴግ በአንድ በኩል ተቃዋሚዎች ህዝብን በሀሰት ፕሮፓጋንዳ እየቀሰቀሱብኝ ነው በማለት ቢናገርም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድህነትና ሁዋላ ቀርነት፣ የኑሮ ውድነትና በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታየው በአቋራጭ የመበልጸግ እና የመልካም አስተዳዳር ችግሮች ስርአቱን የሚፈታተኑ ችግሮች ሆነዋል በማለት እርስ በርሱ የሚጋጭና እራሱን የሚያጋልጥ መግለጫ አውጥቶአል።

ኢህአዴግ የመልካም አስተዳዳር እጦት፣ የኑሮ ውድነትና ስርአጥነት የመሳሰሉት ችግሮች የስርአቱ ፈተና ሆነዋል በማለት ለማመን ከተገደደ፣ በውጭ የሚገኙ ተቃዋሚዎች እነዚህን ችግሮች ያራግባሉ በማለት ክስ ማሰማቱ እርስ በርስ የሚቃረን ነው ሲል ዘጋቢያችን ገልጧል። እነዚህ ችግሮች ባይኖሩና ተቃዋሚዎች ፈጥረው ቢያወሯቸው የኢህአዴግ ወቀሳ ትክክል ይሆን ነበር የሚለው ዘጋቢያችን፣ አሁን ግን ኢህአዴግ ችግሮች በስፋት መኖራቸውን ካመነ በሁዋላ ተቃዋሚዎች እነዚህን ችግሮች እያራገቡ ነው በማለት ክስ መሰንዘሩ ኢህአዴግ የገባበትን አጣብቂኝ ያሳያል ተብሎአል።

የሥርአቱ ቁንጮ መለስ ዜናዊ የዘንድሮውን የግንቦት20 በአል አስመልክቶ ምንም ቃል አልመተንፈሱ ወይም ሁሌም በየአመቱ ያደርግ እንደነበረው በቴሌቪዥን ወይም በራዲዮ ቀርቦ ቃለምልልስ አለማድረጉ እያየለ በመጣበት ተቃውሞ ምክንያት ፋታ ማጣቱን የሚያረጋግጥ ነው ተብሎአል።

መለስ በቅርቡ አመሪካ ላይ በጋዜጠኛ አበበ ገላው ከደረሰበት ውርደት ሳያገግም ደቡብ አፍሪካ ላይ ሌላ ተቃውሞ ተነስቶበት የተጋበዘበት ስብሰባ መሰረዙ ይታወቃል። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ወደ ስልጣን ኮርቻ ያመጣውን ግንቦት20 ለመዘከር አለመቻሉ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል ሲል ኢሳት ዘግቦአል።

## ደቡብ አፍሪካ ውስጥ መለስ ዜናዊን በተናጋሪ እንግዳነት ጋብዞ የነበረው የታቦ ኢምቤኪ የአፍሪካ አመራሪ እንስቲቱይት

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መሰኘታቸዉን በኩራት ገልፀዋል ብሎአል።

የኢትዮጵያ መሪ ነኝ ባዩ መለስ ዜናዊ አንድ ሳምንት በማይሞላ ግዜ ዉስጥ አሜሪካና አፍሪካ ዉስጥ የገጠመዉ ከፍተኛ ተቃዉሞና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደረሰበት የፖለቲካ ክስረት ጌቶቹን ምዕራባዉያንን ጭምር ማስደንገጡ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች የሚስማሙበት ጉዳይ ነዉ።

በሌላ በኩል ደግሞ መለስ ዜናዊ እንደ በቅሎ የደነበረበት የዋሺንግተን ዲሲዉ ስብሰባና አሁን ደግሞ ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ በተጋበዘበት ስብሰባ ላይ አታስፈልግም መባሉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ትልቅ የመነጋገሪያ አርዕስት ሆኖ ሰንብቷል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org